**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Xaphoomu Seeru Allaalsha**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ**

**Sidaama National Regional State Attorney General**

Kiiro /q|_R¼____________________

Barra /qN¼______________________

**SDQM Pirezidaantichu Borro Minira**

**<u>Hawaasa</u>**

**Hajo: <u>Biddi Assinoonninna Wonsinoonni Wodho Sowa Ikkitanno</u>**

SDQM Jeefisiisaanote Amaale Mini Bocaasa 29/2014 M.D hanaffe loosu iima hossanno gede wonsinonna hasiissannore biddi assinoonni **Investimentete Loosira Hossanno Baadiyyete Baatto Wodho Kiiro 18/2014** attamma geeshsha lamu afiinni (sidaamunna amaaru afiinni) qixxaabinota hajo la'anonsa bissa horonsidhanno gede ki'ne widoonni tuqqanno gede assinara ayyirinyunni xa'mineemmo.

**Keerunni!**

**<u>Affino</u>:**

- Qaru Xaphoomu Seeru Allaalaanchira
- Seeru Hajjubba Handaarira
- Jaddotenna Fitihabeerete Hajubba Handaarira
- Gashshootunna Faynaansete Handaarira
- Seeru Xiinxallonna Safote Seeri Qixaawo Dayrekitoreetera

  **<u>X/S/A</u>**

- SDQM Daddalunna Industirete Biirora
- " " Investmentete Komishiinera

  **<u>Hawaasa</u>**

# SIDAAMU DAGOOMU QOQQOWI MOOTIMMA AFFINI GAAZEEXA

## የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አፍኒ ጋዜጣ

## SIDAAMA NATIONAL REGIONAL STATE AFFINI GAZETA

2ki Diro Kiiro 18

Hawaasa, Bocaasa 29, 2014 M.D

Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Amaalete Mini Allaalshi Hundaanni Fulinoho

በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

፪ኛ ዓመት ቁጥር ፲፰

ሀዋሳ፣ ህዳር ፳፱ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም



**Amado**

**Wodhote Kiiro 18/2014**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Investimentete Loosira Hossanno Baadiyyete Baatto Wodho ……… Qoola ….**

**ማውጫ**

**ደንብ ቁጥር ፲፰/፳፻፲፬**

**በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ለኢንቨስትመንት ተግባር የሚውል የገጠር መሬት ደንብ ………… ገጽ…**


**Wodhote Kiiro 18/2014**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Investimentete Loosira Hossanno Baadiyyete Baatto Wodho**

Qoqqowu bayriidi seerira baattote annimma mootimmannitanna dagannita ikkase xawinsoonnihu agaramino gede hee'reenna dureeyye seerunni gumulloonni garinni baadiyyete baatto horonsi'rate qoosso afidhe addi addi investimentete hadaarira bobbakke qoqqowunna goboomu ikonome giddo qeechansa ledanno gede injo kalaqa hasiissannohura,

**ደንብ ቁጥር ፲፰/፳፻፲፬**

**በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ለኢንቨስትመንት ተግባር የሚውል የገጠር መሬት ደንብ**

በክልሉ ሕገ መንግሥት የመሬት ባለቤትነት የመንግሥትና የሕዝብ እንደሆነ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሀብቶች በሕግ በተወሰነው መሰረት የገጠር መሬትን የመጠቀም መብት አግኝተው በተለያዩ የኢንቨስትመንት መስኮች በመሰማራት በክልሉና በሀገራዊ ኢኮኖሚ ውስጥ አስተዋጾ እንዲያበረክቱ ምቹ ሁኔታ መፍጠር በማስፈለጉ፣


**Mittu Waagi ….**
**ያንዱ ዋጋ**

AFFINI GAAZEEXI P.S.K …..
አፍኒ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. …..
Web address: www.affinigazet.gov.et

Baadiyyete baatto gashshoote lainohunni fulino xaphooma seera kaima assatenni baadiyyete baatto dureeyyete sayinsanni gara, horonsi'nanni, qollanni hattono xaphooma gashshootu hajubba muranno tittirshu seera fushsha hasiissannohura,

Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Jeefisiisaanote Amaale Mini Qoqqowu Bayriidi Seeri quwa 57 cinaancho quwa 6 garinni tenne wodho fushshinno.

## GAFA MITE

## Xaphooma Woro

1. **Harancho Umo**

   Tenne wodho "Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Investimentete Loosira Hossanno Baadiyyete Baatto Wodho Kiiro 18/2014" yine xawisa dandiinanni.

2. **Tiro**

   Qaalu horo wole tiro uytannota ikka hoogguro tenne wodho giddo:

   1. **"Qoqqowo"** yaa Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimmaati;
   2. **"Baadiyyete Baatto"** yaa maazagaajju mini amadooshshi gobbaanni woy seerunni quchumaho yine amandoonnikki baattooti;
   3. **"Baattote Kiri Baatooshshi Bikka''** yaa qoqqowu mootimma muro uytanno garinni dureeyye baadiyyete baatto horonsi'rate baattanno baatooshshi bikkaati;
   4. **"Borde''** yaa Sidaamu Dagoomu Qoqqowi

የገጠር መሬት አስተዳደርን በሚመለከት የወጣውን አጠቃላይ የሕግ ማዕቀፍ መነሻ በማድረግ የገጠር መሬት ለባለሀብቶች ስለሚተላለፍበት ሁኔታ፣ ስለአጠቃቀም፣ ስለአመላለስ እንዲሁም ስለአጠቃላይ አስተዳደር ጉዳዮች የሚወስን ዝርዝር የሕግ ማዕቀፍ ማውጣት በማስፈለጉ፣

የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት መስተዳድር ምክር ቤት በክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፯ ንዑስ አንቀጽ ፮ መሰረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ "የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ለኢንቨስትመንት ተግባር የሚውል የገጠር መሬት ደንብ ቁጥር ፲፰/፳፻፲፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጥ ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

   1. **"ክልል"** ማለት የሲዳማ ብሔራዊ ክልል ነው፤
   2. **"የገጠር መሬት"** ማለት ከማዘጋጃ ቤት ወይም አግባብ ባለው ሕግ ከተማ ተብለው ከተከለሉ ክልሎች ውጭ የሚገኝ ማንኛውም መሬት ነው፤
   3. **"የመሬት ኪራይ ክፍያ መጠን"** ማለት የክልሉ መንግስት በሚወስነው መሰረት ባለሀብቶች የገጠር መሬት ለመጠቀም የሚከፍሉት ክፍያ መጠን ነው፤

Mootimma investimentete bordeeti;

5. **“Komishiine”** yaa Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Investimentete Komishiineeti;
6. **“Kira Aannohu’’** yaa qoqqowu investimentete komishiineeti;
7. **“Kiranyu’’** yaa investmentete loosira beeqqo assanno dureessaati;
8. **“Investimente Jeefisiisaano Komite’’** yaa zoonete, woraddate woy quchummate gashshootira investimente lainohunni tittirshu hajo iima gumulote kaa’litanno hedo burqisate uurrinsanni bisooti.

**3. Koo-teemmate Xawishsha**

Tenne wodho giddo mitte koo-teemmanni xawinsonnihu wole koo-teemmanno hanqafanno.

**4. Jeefishshu Mami-Geeshsha**

Tini wodho shiilonna nadaaje hasate, xiinxallotenna fushshate gobbaanni no baalante investimentete loossara jeefishshu noosi.

## GAFA LAME

## Investimentete Loosira Baatto Xa’manna Aa

**5. Baatto Xa’mo**

Aye dureessi investimentete loosira hossannota baadiyyete baatto xa’miranno woyite:

4. **“ቦርድ”** ማለት የክልሉ የኢንቨስትመንት ቦርድ ነው፤
5. **“ኮሚሽን”** ማለት የክልሉ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ነው፤
6. **“አከራይ”** ማለት የክልሉ የኢንቨስትመንት ኮሚሽን ነው፤
7. **“ተከራይ”** ማለት በኢንቨስትመንት ስራ ተሳትፎ የሚያደርግ ባለሀብት ነው፤
8. **“የኢንቨስትመንት አስፈጻሚ ኮሚቴ”** ማለት በዞን፣ በወረዳ ወይም በከተማ አስተዳደር ኢንቨስትመንትን በተመለከተ በዝርዝር ጉዳይ ላይ ለውሳኔ የሚረዳ ሀሳብ እንዲያመነጭ የሚቋቋም አካል ነው፡፡

**3. የጾታ አገላለጽ**

በዚህ ደንብ ውስጥ በአንድ ጾታ የተገለጸው ሌላኛውንም ጾታ ያካትታል፡፡

**4. የተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ ደንብ በማዕድንና ነዳጅ ፍለጋ፣ ምርምርና ማምረት በስተቀር በሁሉም የኢንቨስትመንት ሥራዎች ላይ ተፈጻሚነት አለው፡፡

## ክፍል ሁለት

## ለኢንቨስትመንት ተግባር መሬት ስለመጠየቅ እና ስለማስተላለፍ

**5. መሬት ስለመጠየቅ**

ማንኛውም ባለሀብት ለኢንቨስትመንት ተግባር የሚውል የገጠር መሬት ሲጠይቅ፡-

1. Komishiinetenni qixxaabino xa’mo shiqishate qitse umisinni woy seeru garinni lekkisaminohunni wonshateninna malaatisatenni;
2. Loosate hedino investimentete loosi daafira harancho pirojekitete xawishshi taje;
3. Pirojekitesiha 30% kapitaale leellishshannota baankete tajenna
4. Investerichu ayyimma xawisanno taje (afamooshshu kaarde woy paasi poorte woy Galtinote wodhonna uurrisate wodho wkl) koppe abba noosi.

## 6. Baatto Aa

1. Komishiine tenne wodho quwa 5 garinni shiqanno sanadubba amadonna seeru garimmase keenatenni gumulote hedo qixxeessatenni jeefisiisaanote amaale minira shiqishshanno.
2. Jeefisiisaanote amaale mini shiqqino baattote xa’mo seerunna gashshootu hajubba raginni tittirshu qorqorsha assatenni gumulo aanno.
3. Konni quwi cinaanchu quwi 2 garinni baatto uynannisi gede gumulloonisi dureessi mittu agani giddo komishiinete ledo sheemaate eannoha ikkanna konni garinni e’nonni sheemaati sanade buuxatenna borreessate biilloonyi no bisiwa borressama noosi.
4. Konni quwi cinaanchu quwi 3 garinni sheemaate eino durreessi:
   a) Tenne wodho ledo maqinsonni investmentete handaarita baattote kiri

1. በኮሚሽኑ የተዘጋጀውን የመጠየቂያ ቅጽ በራሱ ወይም በሕጋዊ ወኪሉ በመሙላትና በመፈረም፤
2. ሊሰራ ያሰበውን የኢንቨስትመንት ሥራ የሚገለጽ አጭር የፕሮጀክት ማብራሪያ ሠነድ፤
3. የፕሮጀክቱን 30% (ሰላሳ ከመቶ) ካፒታል የሚያሳይ የባንክ ሰነድ እና
4. የኢንቨስተሩን ማንነት የሚገልጽ ሰነድ (መታወቂያ ካርድ ወይም ፓስፖርት ወይም መተዳደሪያ ደንብና መመስረቻ ጽሁፍ ወዘተ.) ኮፒ ማቅረብ አለበት፡፡

## 6. መሬት ስለማስተላለፍ

1. ኮሚሽኑ በዚህ ደንብ አንቀጽ 5 መሰረት የቀረቡ ሠነዶችን ይዘትና ሕጋዊነትን በመገምገም የውሳኔ ሀሳብ በማዘጋጀት ለመስተዳድር ምክር ቤት ያቀርባል፡፡
2. መስተዳድር ምክር ቤት የቀረበውን የመሬት ጥያቄን ከሕጋዊና ከአስተዳደራዊ ጉዳዮች አንጻር በዝርዝር በመመርመር ውሳኔ ይሰጣል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት መሬት እንዲሰጣው የተወሰነለት ባለሀብት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የውል ስምምነት ከኮሚሽኑ ጋር የሚፈራረም ሲሆን በዚህ መልኩ የተደረገ የውል ስምምነት ሥልጣን ባለው ሰነድ አረጋጋጭና መዝጋቢ አካል ዘንድ መመዝገብ አለበት፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት የውል ስምምነት የገባ ባለሀብት:-
   ሀ) ከዚህ ደንብ ጋር አባሪ በተደረገው የኢንቨስትመንት ዘርፉ የመሬት ኪራይ ተመን መሰረት ከአጠቃላይ የውል ዘመኑ

bikka xaphoomu sheemaatu dirinni bocunniha baatote kira balaxe baatannoha ikkanna gatino kira gattino liizete dirrara bebbeenkeenna baatanno,

b) Xaphoomu sheemaatu diriha temberete qaraxonna woloota seerunni murronni baatooshshubba jeefisanno,

c) Konni cinaanchu quwi fidale “a” nna “b”ra woroonni hajubba jeefisasi xawisanno sanadubba komishiinete shiqishiro mittu agani giddo kaarta, amadote xawishshi woraqatanna baattote amado albunni marre sayinsanniha ikkanno.

5. Investmentete saynse uynoonni amado giddo hattene investmentete danira ikkitannokki amadote kifile tuncu yitannoha ikkiro amadote buuxishshi sanadubba iima taashshate looso loosatenni garumma noo hajora hosanna gede assinanni. Tittirshu jeefishsha komishiine fushshitanno biddissinni xawinsara dandiinanni.

## GAFA SASE

## Sheemaatu Amado

### 7. Sheemaatu Sanade Xaphooma Amado

Aye dureessi komishiinete ledo e’anno baatto karaaya’ate sheemaati ajanni ajeenna konni woroonni xawinsonni bixxillubba amadinoha ikka noosi:

የግማሹን መሬት ኪራይ አስቀድሞ የሚከፍልና ቀሪውን ክፍያ ለቀሪ የሊዝ ዓመታት ተሸንሽኖ ይከፍላል፤

ለ) የአጠቃላይ የውል ዘመኑን የቴምበር ቀረጥ እና ሌሎች ሕጋዊ ክፍያዎችን ይፈጽማል፤

ሐ) በዚህ ንዑስ አንቀጽ በፊደል ተራ “ሀ” እና “ለ” የተመለከቱ ተግባራትን መፈጸሙን የሚያረጋገጥ ሰነድ ለኮሚሽኑ ስያቀርብ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ካርታ፣ የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እና በመስክ ይዞታውን የማስተላለፍ ተግባር የሚፈጸም ይሆናል።

5. ለኢንቨስትመንት ተላልፎ በተሰጠ ይዞታ ውስጥ ለዚያ የኢንቨስትመንት ዓይነት የማይሆን የይዞታ ክፍል ያጋጠመ እንደሆነ የይዞታ ማረጋገጫ ሠነዶች ላይ ማስተካከያ በማድረግ አግባብነት ላለው ተግባር እንዲውል ይደረጋል። ዝርዝር አፈጻጸም ኮሚሽኑ በሚያወጣ መመሪያ ሊገለጽ ይችላል።

## ክፍል ሦስት

## ስለውል ይዘት

### 7. የውል ሰነዱ አጠቃላይ ይዘት

ማንኛውም ባለሀብት ከኮሚሽኑ ጋር የሚገባው የመሬት ኪራይ ውል ቢያንስ ከዚህ በታች የተመለከቱ ነጥቦች የያዘ መሆን አለበት፡-

1. የተዋዋይ ወገኖችን ሙሉ ስምና አድራሻ፤
2. የመሬቱን ደረጃና የሚገኝበትን አድራሻ፤
3. የኢንቨስትመንት ዘርፉንና የተፈቀደውን የይዞታ

1. Sheemaate eino bissa wo’ma su’manna teesso;
2. Baattote deerranna afantanno teessso;
3. Investimentete handaaranna fajjinoonni amadote bikka;
4. Investmentete looso xawisanno haranchu xawishshi;
5. Baattote kiri bikkanna baantanni gara;
6. Sheemaate eino bissa qoossonna gadacho;
7. Sheemaatu keeshshanno yanna, haaroonsinaninna diinganni gara;
8. Sheemaatu galanno seeranna kipho tiranni gara;
9. Baatto sayinsanni garanna latisate pirogiraame;
10. Sheemaate sidaamu afiininna sheemaate e’anno bissa sumummenni ledote afuubbanni assinara dandiinanni.

**8. Sheemaatu Yanna**

Addi addi investimentete loosira fajjinoonni jawiidi baattote kiri sheemaati yanna tenne wodho ledo maqinsonni shae “A” garinni ikkanno.

**9. Kiru Bikka**

1. Investimentete loosira hossanno baadiyyete baatto kiri bikki tenne wodho ledo maqinsonni shae “B” nna “C” aana worroonni garinni ikkanno.
2. Konni quwi cinaanchu quwi 1 aana xawisoonnihu baattote kiri bikki woradu

መጠን፤

4. የኢንቨስትመንት ሥራውን የሚገልጽ አጭር ማብራሪያ፤
5. የመሬት ኪራይ መጠን እና ስለአከፋፈል ሁኔታ፤
6. የተዋዋይ ወገኖች መብትና ግዴታ፤
7. ውሉ የሚቆይበትን ጊዜ፣ ስለሚታደስበትና ስለሚሰረዝበት ሁኔታ፤
8. ውሉ ስለሚገዛበት ሕግ እና አለመግባባት ስለሚፈታበት ሁኔታ፤
9. መሬቱ የሚተላለፍበት አግባብ እና የሚለማበት ፕሮግራም፤
10. ውሉ በሲዳሙ አፎ እና በተዋዋይ ወገኖች ስምምነት በተጨማሪ ቋንቋዎች ሊደረግ ይችላል፡፡

**8. የውል ዘመን**

ለተለያዩ የኢንቨስትመንት ዘርፎች የተፈቀደው ከፍተኛ የመሬት ኪራይ የውል ዘመን ከዚህ ደንብ ጋር አባሪ በተደረገው በሰንጠረዥ “ሀ” መሰረት ይሆናል፡፡

**9. የኪራይ መጠን**

1. ለኢንቨስትመንት ተግባር የሚውል የገጠር መሬት ኪራይ መጠን በዚህ ደንብ በሰንጠረዥ “ለ” እና “ሐ” ላይ በተቀመጠው መሰረት ይሆናል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ላይ የተመለከተው የመሬት ኪራይ መጠን እንደየወረዳው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ

dagoomittenna miinju latishshi, baattote shaqqadimma, dikkote ikkito, baattote bikka, dagate buusammenna labbanno hajubba kaima assitino xiinxallonni ontu dirinni ajannokki yannanni borde fushshitanno biddissinni woyyeessa dandiinanni.

3. Pirojekitete akatinna qoqqowu lophora fultanno qeechi garinni la'nanni baattote kira baatate yanna seedisatenni jawaachishsha uyinara dandiinanni. Tittirshu jeefishsha borde fushshitanno biddissinni gumullanni.
4. Kiru bikka shallagate horote hossannonna tenne wodho ledo maqinsonni shae "B" iima xawinsonninna mittu woradi giddo heedhanno baatto deerra yannilicho xiinxallo, xawonna hedate dandiisanno bikaancho kaima assatenni komishiine fushshitanno biddisinni muranniha ikkanno.

**10. Sheemaate Jeefisate Assa Hasiissanno Qoropho**

Kira aate xa'minoonni qarqarira danna xaaddannotinna lattannoti jawa baatto noota buunxiro sheemaate eate albaanni:

1. Dureessaho uynanni baatto konni ka'ira qarqaru baatto wolu latishshira hosiisate ittissannokkita ikkase;
2. Baatto horoonsi'rate pilaane loosantino qarqara ikkiro pilaanete garinni ikkase;
3. Baci-lubbote tuqishshinna wole qarqaru jiro lainohunni addi waaga afidhino baatto

ልማት፣ የመሬት ልስላሴ፣ የገበያ ሁኔታ፣ የመሬት መጠን፣ የህብረተሰቡን ትብብርና የመሳሰሉ ጉዳዮችን መነሻ ባደረገ ጥናት ከአምስት ዓመት ባላነሰ ጊዜ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ሊሻሻል ይችላል።

3. የፕሮጀክት ባህሪንና ለክልሉ ዕድገት ከሚያበረክተው አስተዋጾ አንጻር እየታየ የመሬት ኪራይ የመክፈያ ጊዜን የማራዘም ማበረታቻ ሊሰጥ ይችላል። ዝርዝር አፈጻጸሙ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።
4. ለኪራይ መጠን ስሌት የሚያገለግለውን እና ከዚህ ደንብ ጋር አባሪ በተደረገው ሠንጠረዥ "ለ" ላይ የተመለከተውንና በአንድ ወረዳ ውስጥ የሚገኝ የመሬት ደረጃን ወቅታዊ ጥናትን፣ ግልጽና ተገማች መስፈርትን መነሻ በማድረግ ኮሚሽኑ በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰን ይሆናል።

**10. ውል ለማስፈጸም መደረግ ያለበት ጥንቃቄ**

ኪራይ ለመስጠት በተጠየቀው አካባቢ በዓይነት የሚገናኝና የሚለማ ሰፊ መሬት መኖሩ ከተረጋገጠ ውል ከመገባቱ በፊት፡-

1. ለባለሀብቱ የሚሰጠው የመሬት ኪራይ ውል ከዚህ በኋላ የአካባቢውን መሬት ለሌላ ልማት ለማዋል የማያግድ መሆኑን፣
2. የመሬት አጠቃቀም ፕላን የተሰራበት አካባቢ ሲሆን በፕላኑ መሰረት መሆኑ፣
3. የብዝሃ-ሕይወት ስርጭትና ሌሎች ከአካባቢ ሀብት አኳያ የተለየ ዋጋ ያለውን መሬት የለየ መሆኑን ማጠን ያስፈልጋል።

badinoha ikkasi huwata hasiissanno.

## GAFA SHOOLE

**Sheemaate Eanno Bissa Qoossonna Gadacho**

**11. Kiranyu Qoosso**

1. Investimentete daninna hala'linyi garinni haja la'annonsa uurrinshubba ledo amaalamanni loosisi'ranna loosaasinesira ikkitanno biiro, gallanni minna, nadaajete tuqishsha, fayyimmatenna rosu minna loosate dandaanno.
2. Baatto umisinni woy lekkisaanchunni latisatenna gashshate dandaanno.
3. Haja la'anosiha mootimmate loosu minna fajjisiisi'renna hatenne hajara fulitino seeru harinsho harunsatenni loosisira hasiissanno kofatto, gorsa bo'e, doogo, buusa w.k.l. xintu latishshi ijaara loosate, horoonsi'ratenna mootimmate irko xa'mirate qoosso noosi.

**12. Kiranyu Gadacho**

1. Adhino baattonna baattote aana noo jiro agarate gadacho noosiha ikkanna addintanni:
   a) Irshu loosira injeessate yine maxarranni haqqe riqiwatenni wole haqqe kaasanna owaata;
   b) Bushshu hoshooshammera reqecci yitino bagaame basera bushshu hoshooshama hoolate sumuu yitanno hayyo

**ክፍል አራት**

**የተዋዋይ ወገኖች መብትና ግዴታ**

**11. የተከራይ መብት**

1. በኢንቨስትመንቱ ዓይነትና ስፋት መሰረት ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር እየተማከረ ለሥራውና ለሰራተኞቹ የሚሆን ቢሮ፣ ማደሪያ ቤቶች፣ የነዳጅ አቅርቦት፣ የጤናና ትምህርት ቤቶችን መስራት ይችላል፡፡
2. መሬቱን በራሱ ወይም በተወካዩ ማልማትና የማስተዳደር ይችላል፡፡
3. ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶችን አስፈቅዶና ለዛ ጉዳይ የወጣ ሕጋዊ አሰራርን በመከተል ለስራው የሚያስፈልግ ግድብ፣ የመስኖ ቦይ፣ መንገድ፣ ድልድይና ወዘተ. መሰረተ ልማት መገንባት፣ መጠቀም እንዲሁም የመንግሥትን ድጋፍ መጠየቅ ይችላል፡፡

**12. የተከራይ ግዴታ**

1. የተላለፈለትን መሬትና በመሬቱ ላይ ያለውን ሀብት የመንከባከብ ግዴታ ያለበት ሲሆን በተለይም:-
   ሀ) ለእርሻ ስራ ለማመቻቸት በማለት ለሚመነጠር እንጨት በምትኩ ሌላ እንጨት መትከልና መንከባከብ፤
   ለ) ለአፈር መሸርሸር የተጋለጡ ተራራማ ቦታዎች የአፈር መሸርሸርን ለመከላከል ተስማሚ ስልት መጠቀም፣ የተፈጥሮ ሀብት ልማትና ጥበቃን በተመለከተ

horoonsi'ra, kalaqamu jiro latishshanna agarooshshe lainohunni haja la'annosi bisi fushshanno biddissa ayirrise loosa hasiissanno.

2. Baatto adhihunni mittu diri giddo sheemaatisi garinni xaphooma baattosinni 30% (xibunni sajjoo anga) latisa noosi.
3. Adhino baatto shoole diro sainokki yanna giddo gudiseenni latisa noosi. Tenne yanna giddo lattinokki baatto kiiso nookkiha adha dandiinanni.
4. Konni quwira cinaancho quwa 3 aana xawinsoonnihu agarame hee'reenna kira uyhu 6 agani qorophishsha aanosiha ikkanno.
5. Baattote kiri sheemaati yaanna gooffuro woy sheemaatu diigamironna faajjosi yanna goofuro baattote aana noosi jiro seeru garinni kayse baatto kira uysihura 6 agana sa'inokki yanna giddo qolate gadacho noosi.
6. Haja la'annosi bisi investimentete millimillo rippoorte xa'miro halaalanya rippoorte shiqishate gadacho noosi.
7. Baattote kiri baatooshshe amado afantanno gashshootu tantanora heedhanno eote uurrinshara diru dirunkunni Birra 1 kayise Dotteessa 30 geeshsha sheemaatisi garinni baata noosi.
8. Irshu loosira baattoo qixxeessa hasiissanno yannara maxarranni haqqenna wole baattotte aana noo jiro kincho, shaafanna w.k.l. jiro kira uyhuta ikkitinota huwatatenni horonsi'rate hasiisisiro kira uysihura balaxe

ጉዳዩ ከሚመለከተው ክፍል የሚያወጣውን መመሪያ አክብሮ መስራት ያስፈልጋል፡፡

2. መሬቱን ከወሰደ ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በውሉ መሰረት ከጠቅላላ መሬቱ 30% (ሰላሳ ከመቶ) ማልማት አለበት፡፡
3. የወሰደውን መሬት አራት ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ጨርሶ ማልማት አለበት፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ ያልለማ መሬትን ያለካሳ መውሰድ ይቻላል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ላይ የተመለከተው እንዳለ ሆኖ አከራይ የ6 ወር ማስጠንቀቂያ የሚሰጠው ይሆናል፡፡
5. የመሬት ኪራይ ውል ጊዜ ካለቀ ወይም ውሉ ከፈረሰና የፍቃድ ዘመኑ ካበቃ በመሬቱ ላይ ያለውን ሀብት በሕግ አግባብ አንስቶ መሬቱን ለአከራይ 6 ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የመመለስ ግዴታ አለበት፡፡
6. ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ሪፖርት ሲጠየቅ እውነተኛ ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡
7. የመሬት ኪራይ ክፍያውን ይዞታው በሚገኝበት አስተዳደር መዋቅር ለሚገኝ የገቢ ተቋም በየዓመቱ ከጥቅምት 1 እስከ ሚያዝያ 30 ባሉ ጊዜያት በውሉ መሰረት መክፈል አለበት፡፡
8. ለእርሻ ስራ መሬት ማዘጋጀት በሚያስፈልግበት ጊዜ የሚመነጠር እንጨትና ሌላ በመሬቱ ላይ ያለን ሀብት ዲንጋይ፣ አሸዋና ሌሎች ይህን የመሳሰሉ ሀብቶች የአከራይ መሆናቸውን በመገንዘብ መጠቀም ካስፈለገው ለአከራይ አስቀድሞ በማሳወቅ

egensiisatenni fajjishiishiranna hasiisanno baatooshsheno baata noosi.

9. Adhino baatto aana loosate mixi'rino pirojekite calla loosa noosi. Pirojekitete dana soorra hasi'riro haja la'anno bisi ledo balaxe hasaawe soorrate sumuumme afi'ra noosi.
10. Investmente loossanno qarqarira heeranno dagooma horaameessa assitanno addi addi latishshu loossa loosa noosi.

**13. Kira Aannohu Gadacho**

1. Kira aannohu sheemaate eino kiranyira tenne wodho quwa 6 garinni baatto kiranyaho sayise aa noosi.
2. Kiranyu eino sheemaati garinni gadachosi ayirrise loosasi ha'runsa noosi.
3. Konni quwira cinaancho quwa 2 garinni assinanni ha'runsonna qorqorshi kiranyu loosi millimillo aana ittishsha kalaqannokki gede qoropho assa hasiissanno.
4. Sheemaatu kaajje keeshshanno yanna giddo kiranyu adhino baatto ga'labbote qarri nookkiha loosanno gedenna horoonsi'ranno gede sayikki woganenni ka'annota qoossote mereero eate ikkitubba gargaratenna woowe aate gadacho noosi.
5. Dureessu woy kiranyu gaddachosi agaranna ayirrisa hoogiro sheemaatu diigameenna hasiissanno harinsho hanafanno gede loosa noosi.

ማስፈቀድና አስፈላጊውን ክፍያ መፈጸም አለበት፡፡

9. በወሰዳው መሬት ላይ ለመስራት ያቀደውን ፕሮጀክት ብቻ መስራት አለበት፡፡ የፕሮጀክቱን ዓይነት መቀየር ከፈለገ ጉዳዩ ከሚመለከተው አካል ጋር አስቀድሞ በመነጋገር የመቀየር ስምምነት ማግኘት አለበት፡፡
10. ኢንቨስትመንቱን በሚያከናውንበት አካባቢ የሚኖረውን ህብረተሰብ ተጠቃሚ የሚያደርጉ የተለያዩ የልማት ተግባራትን ማከናወን አለበት፡፡

**13. የአከራይ ግዴት**

1. አከራይ የውል ስምምነት ለተፈራረመው ተከራይ በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 መሰረት መሬቱን ለተከራይ አስተላልፎ መስጠት አለበት፡፡
2. ተከራይ በገባው ውል መሰረት ግዴታውን አክብሮ መስራቱን መከታተል አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት የሚደረግ ክትትልና ምርመራ ተከራይ የስራ እንቅስቃሴው ላይ እክል እንዳይፈጥርበት በጥንቃቄ ማድረግ አለበት፡፡
4. ውሉ ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ ውስጥ ተከራይ የወሰደውን መሬት የፀጥታ ችግር በሌለበት ሁኔታ እንዲሰራና እንዲጠቀም ከሶስተኛ ወገን የሚነሳ በመብት ላይ የሚደረግ ጣልቃ ገብነትን የመከላከልና ዋስትና የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡
5. ተከራይ ግዴታውን መጠበቅና ማክበር ካልቻለ ውሉ ፈርሶ አስፈላጊ ሂደቶች እንዲጀመሩ መስራት አለበት፡፡

## GAFA ONTE

## Sheemaatu Diigamanno Korkaatanna Ha'rinsho

### 14. Sheemaatu Diigamanno Korkaati

Baadiyyete baattohu kiru sheemaati konni woroonni noo korkaatubbanni mittu heeriro diigamara dandaanno:

1. Kira uyhu kiranyaho wolqate ale ikkino korkaatinni baatto sayse aa hoogiro;
2. Kiranyu sheemaate e''e adhino xaphooma baatto mittu diri giddo ajay ajeenna 30% (sajjo anga) latisa hoogiro;
3. Kiranyu baattote baatooshshi kira lame aantete diro baatikki keeshshiro;
4. Baattote kiri sheemaati aana bande xawisoonni gadacho ayirrisa hoogironna wole konne lawino korkaatinnii.

### 15. Sheemaate Diigate Ha'rinsho

1. Sheemaate e'u lamente wogane sumuummenni woy lamunku mittu shiqishshanno xa'monni diiga dandiinanni.
2. Baattote kiri sheemaati diigamara hasi'rihu diigara umo asse 6 agani qorophishsha aa noosi.
3. Baattote kiri sheemaati diigamiro kiranyu kira uysihura sheemaatu diigamihunni hanafe 6 agani giddo baatto qole aa noosi.
4. Kira uyhu aanno qorophishshi kiranyu baattote aana noosi laalcho gamba assi'ranno

## ክፍል አምስት

## ውል ስለሚፈርስበት ምክንያት እና አካሄድ

### 14. ውል የሚፈርስበት ምክንያት

የገጠር መሬት የኪራይ ውል ከዚህ በታቾ ከተዘረዘሩት ምክንያቶች አንዱ ከተሟላ ሊፈርስ ይችላል፡-

1. አከራዩ ለተከራይ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሬቱን አስተላልፎ መስጠት ካልቻለ፤
2. ተከራይ ውል ገብቶ ከወሰደው ጠቅላላ መሬት በአንድ ዓመት ውስጥ ቢያንስ 30% (ሰላሳ ከመቶ) ማልማት ካልቻለ፤
3. ተከራይ መሬቱን የተከራየበትን ክፍያ ለሁለት ተከታታይ ዓመታት ሳይከፍል ከቆየ፤
4. በመሬት ኪራይ ውል ላይ ተለይቶ የተቀመጠ ግዴታ ማክበር ካልቻለና በሌሎች ተመሳሳይ ምክንያቶች።

### 15. ውል የሚፈርስበት ሂደት

1. በሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች ስምምነት ወይም ከሁለቱ አንዱ በሚያቀርበው ጥያቄ ማፍረስ ይቻላል።
2. የመሬት ኪራይ ውሉ እንዲፈርስ የፈለገ ወገን ውሉ ከመፍረሱ አስቀድሞ የ6 ወር ማስጠንቀቂያ መስጠት አለበት።
3. የመሬት ኪራይ ውል ከፈረሰ ተከራይ ለአከራይ ውሉ ከፈረሰ ጀምሮ በ6 ወር ውስጥ መሬቱን መልሶ መስጠት አለበት።
4. አከራይ የሚሰጠው ማስጠንቀቂያ ተከራይ መሬቱ ላይ ያለውን ምርት የሚሰበስብበትን ጊዜ ግምት ውስጥ ያስገባና መሬቱ ላይ

yanna hedote giddo woranna baattote aana latishshaho hosiisate yee fushshi’rinoti wole fulote qixxaawo nookki yanna hedote giddo worreeti.

5. Konni quwira cinaancho quwa 4 garinni sheemaate jeefisate qarra ikkeenna diinganni wote baatote aana iillinokki gidi woy laalchi woy wolu latishshu loosi hee’riha ikkiro kiranyu baatto gawajjannokki garinni kaysa dandaanno.
6. Kira uyihu uyno qorphishshu yanna giddo kiranyu jirosi kayse baatto kira uysihura qola hoogiro kira uyhu baattote aana noo jiro investimentete jeefisiisaano komite gaantanno ogimmate komitenni borreessante amadantanno gede assinihu gedensaanni mootimmate eo asse hajo lainohunni poolisete egensiisatenni baatto hasi’noonni hajara hosiisa dandiinanni.

## GAFA LEE

## <u>Addi Addi Woro</u>

### 16. Amadooshshu Qoosso Woowete Amadisiisanna Saykki Woganera Sayisa

1. Baadiyyete baatto horoonsi’rate uynoonnisihu aye dureessi baattote aana kalaqi’rino jiro sheemaatisi diri giddo woowe asse amadisiisate qoosso noosi.
2. Baadiyyete baatto horoonsi’rate qoosso

ለልማት ለማዋል ብሎ ያወጣውን ሌላ የወጪ ዝግጅት የሌለበትን ወቅት ግምት ውስጥ አስገብቶ መሆን አለበት፡፡

5. በዚህ አንቀጸ ንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት ውሉን ለመተግበር አስቸጋር ሆኖ በሚፈርስበት ወቅት በመሬቱ ላይ የነበረው ያልደረሰ አህል ወይ ሰብል ወይም ሌላ የልማት ስራ ያለ ከሆነ ተከራይ መሬቱን በማይጎዳ መልኩ ማንሳት ይችላል፡፡
6. አከራይ የሰጠው የማስጠንቀቂያ ጊዜ ውስጥ ተከራይ ሀብቱን አንስቶ መሬቱን ለአከራይ ያልመለሰ እንደሆነ በመሬቱ ላይ ያለውን ሀብት አከራይ በኢንቨስትመንት አስገፈጻሚ ኮሚቴ በሚመደቡ የባለሙያዎች ኮሚቴ አማካኝነት ተመዝግቦ እንዲያዝ ከተደረገ በኂላ ለመንግስት ገቢ አስደርጎ ጉዳዩን ለፖሊስ አሳውቆ መሬቱን ለሚፈለገው ጉዳይ ማዋል ይችላል፡፡

## ክፍል ስድስት

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋዎች</u>

### 16.የይዞታ መብትን በዋስትና ስለማስያዝ እና ለሦስትኛ ወገን ስለማስተላለፍ

1. የገጠር መሬት እንዲጠቀም የተሰጠው ማንኛውም ባለሀብት በመሬቱ ላይ ያፈራውን ሀብት በውል ዘመኑ ዋስትና አድርጎ የማስያዝ መብት አለው፡፡
2. የገጠር መሬት የመጠቀም መብት የተሰጠው ማንኛውም ባለሀብት ፕሮጀክቱ ፍሬ የመስጠት ደረጃ ከመድረሱ በፊት ለሶስተኛ ወገን

uynoonnisihu aye dureessi pirojekitesi laalcho aate deerrira e’ukkinni sayikki woganera sayse aa didandaanno. Ikkeennano wolu dureessi ledo seeru garinni qinaawe latisa dandaanno.

3. Konni quwira cinaancho quwa 2 garinni pirojekitesi laalcho aate deerrira reekkantuhu gedensaanni sayikki woganera saysate ajayi ajeenna 50%(ontaa anga) lata noose. Baatto sayinse uyni woganeno albiidi kiranyira noosi gadacho ayirrisa noosi.
4. Baattote kiri kakkayishshu irkishsha horoonsidhino pirojekite sayikki woganera sa’anno woyte uynoonnisiti kakkayishshu irkishshi yanna gooffinokkiha ikkiro sayinse uynisi bisi kakkayishsha horoonsi’noonni latishshi daninni adhe sa”a noosi.
5. Konni quwira cinaancho quwa 1 nna 2 aana xawinsoonnihu agarame hee’reennanni aye dureessi investe assara kirunni adhino baatto sayikki woganera saysate ikko baattote aana kalaqino jiro woowete amadisiisate kiru sheemaati yanna giddo komishiinete shiqe borrotenni fajjishiishira noosi.
6. Sheemaatu diri goofikkinni baattote aana jiro kalaqino dureessi reyha ikkiro seeru garinni baattote amadooshshe ragi’rate qoosso noosi manchira sayinsanni. Ragi’raanchuno albi kiranyi einno gadacho garinni latishsha sufisanno.

አስተላልፎ መስጠት አይችልም፡፡ ሆኖም ከሌላ ባለሀብት ጋር በህግ አግባብ ተቀናጅቶ ማልማት ይችላል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ፕሮጀክቱ ፍሬ መስጠት ደረጃ ከደረሰ በኋላ ለሶስተኛ ወገን ለማስተላለፍ ቢያንስ 50% (ሃምሳ ከመቶ) መልማት አለበት፡፡ መሬቱ ተላልፎ የተሰጠው ወገንም የበፊቱ ተከራይ ያለበትን ግዴታ ማክበር አለበት፡፡
4. የመሬት ኪራይ የማበረታቻ ድጋፍ የተጠቀመ ፕሮጀክት ለሶስተኛ ወገን ሲተላለፍ የተሰጠው የማበረታቻ ድጋፍ ጊዜው ያላለፈበት ከሆነ ተላልፎ የተሰጠው አካል ማበረታቻ በተጠቀመበት የልማት ዓይነት ይዞ መተላለፍ አለበት፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ባለሀብት ኢንቨስት ለማድረግ በኪራይ የወሰደውን መሬት ለሶስተኛ ወገን ለማስተላለፍም ሆነ በመሬቱ ላይ ያፈራውን ሀብት በዋስትና ለማስያዝ በኪራይ ውሉ ዘመን ውስጥ ለኮሚሽኑ ቀርቦ በጽሁፍ ማስፈቀድ አለበት፡፡
6. የውሉ ዘመን ሳያልቅ በመሬቱ ላይ ሀብት ያፈራ ባለሀብት የሞተ እንደሆነ በሕግ መሰረት የመሬት ይዞታው የመውረስ መብት ላለው ሰው ይተላለፋል፡፡ ወራሽም የቀድሞው ተከራይ በገባው ግዴታ መሰረት ልማቱን ይቀጥላል፡፡

**17. Waa Afi'ranna Horoonsi'ra Lainohunni**

1. Haja la'annosihu mootimmate bisi waa horoonsi'rate fushshanno seera kaima asse dureessu baattote iimiidi waa ikko baattote giddonni fushshe horoonsi'ra dandaanno.
2. Gorsu wayinni horoonsi'ra hasi'ranno dureessi balaxe xiinxallosi komishiinetenna waynna gorsu latishshi biirora shiqishe sumuumme afi'ra noosi.

**18. Investimentete Uynannikki Baadiyyete Baatto**

Wolu seerinni addi garinni mura hoongiro xaggetenna amma'note base hojji investimentera diuynanni.

**19. Koffenya Shiqishi'ra**

1. Investmentete hajora komishiinetenni woy wolootta mootimmate uurrinshubbanni uynonni gumulora koffenyu noosi durreessi komishiinete gashshootu koffenyasi borrotenni shiqishira dandaanno.
2. Komishiinetenni uynonni gumulonni kassi yiinokki dureessi gumulo uyninkunni 30 loosu barri giddo kado bordete shiqishira dandaanoha ikkanna coy cu'mo iima borde uytanno gumulo goofimarchunnita ikkitanno.
3. Konni quwi cinaanchu quwi 1 nna 2 worroonnihu heerirono kipho tirate sheemaatunni balanxe murronni hayyo horonsirate qoosso agarantinote.

**17. ውሃ ማግኘትንና አጠቃቀሙን በተመለከተ**

1. ጉዳዩ የሚመለከተው የመንግስት አካል ውሀ መጠቀምን በተመለከተ በሚያወጣው ህግ መሰረት በማድረግ ባለሀብቱ የመሬቱ የላይኛውን ክፍል ውሀ ሆነ የታችኛው ክፍል ውስጥ የሚገኘውን ውሀ አውጥቶ መጠቀም ይችላል፡፡
2. የመስኖ ውሀ መጠቀም የሚፈልግ ባለሀብት አስቀድሞ ጥናቱን ለኮሚሽኑ እና ለውሃና መስኖ ልማት ቢሮ አቅርቦ ስምምነት ማግኘት አለበት፡፡

**18. ለኢንቨስትመንት ስለማይሰጥ የገጠር መሬት**

በሌላ ሕግ በተለየ ሁኔታ ካልተወሰነ በስተቀር ታሪካዊና የእምነት ቦታዎች ለግል ኢንቨስትመንት አይሰጡም፡፡

**19. ቅሬታ ስለማቅረብ**

1. በኢንቨስትመንት ጉዳይ በኮሚሽኑ ወይም በሌሎች መንግሥታዊ ተቋማት በተሰጡ ውሳኔዎች ላይ ቅሬታ ያለው ባለሀብት ለኮሚሽኑ አስተዳደራዊ ቅሬታውን በጽሁፍ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. በኮሚሽኑ በተሰጠ ውሳኔ ያልረካ ባለሀብት ውሳኔው በተሰጠ በ30 የሥራ ቀናት ውስጥ ይግባኝ ለቦርዱ ማቅረብ የሚችል ሲሆን በፍሬ ነገር ላይ ቦርዱ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተመለከተው ቢኖርም ያለመግባባትን ለመፍታት በውል ስምምነት አስቀድሞ የተወሰነውን ዘዴ የመጠቀም መብት የተጠበቀ ይሆናል፡፡

**20. Reekote yanna woro**

Tini wodho fultara albanni assinoonni baadiyyete baatto investimentete sheemaatubba tenne wodho wonsininkunni hanafe mittu diri giddo wodhote garinni hasiisanno woyyeessate looso loonsanniha ikkanno.

**21. Biddissa Fushshate Biilloonye**

Investimentete borde tenne wodhoha xaphooma jeefishsha kaajishate hasiissanno biddissa fushsha dandiitanno.

**22. Jeefishshu Hee'rannosikki Seeranna Assoote**

Tenne wodho ledo kiphi yaanno aye seeri woy rosamino assooti tenne wodhonni hanqafantino hajubba lainohunni jeefishshu dihee'rannosi.

**23. Wodho Loosu Aana Hossanno Yanna**

Tini wodho Bocaasa 29/2014 M.D hanaffe loosu aana hossanno.

**Hawaasa, Bocaasa 29, 2014 M.D**

**Desta Ledamo**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Pirezidaanticha**

**20. የመሸጋሪያ ጊዜ ድንጋጌ**

ይህ ደንብ ከመውጣቱ በፊት የተደረጉ የገጠር መሬት የኢንቨስትመንት ስምምነቶች ይህ ደንብ ከጸደቀበት ጊዜ ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በዚህ ደንብ መሰረት አስፈላጊ ማሻሻያ የሚደረግባቸው ይሆናል፡፡

**21. መመሪያ የማውጣት ስልጣን**

የኢንቨስትመንት ቦርዱ የዚህን ደንብ አጠቃላይ አፈጻጸም ለማጠናከር የሚያስፈልግ መመሪያ ማውጣት ይችላል፡፡

**22. ተፈጻሚነት የሌለው ሕግና አሰራር**

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ ለተሸፈኑ ጉዳዮች ተፈጻሚነት የለውም፡፡

**23. ደንቡ ሥራ ላይ የሚውልበት ጊዜ**

ይህ ደንብ ከህዳር ፳፱ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ ይውላል፡፡

ሀዋሳ፣ ህዳር ፳፱ ቀን ፳፻፲፬ ዓ.ም

**ደስታ ሌዳሞ**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት**

**ርዕሰ መስተዳድር**

**Maqishsha A**

Qoqqowi giddo baadiyyete baatto aana addi addi investimeentete handaarira fajjinoonniha jawiidi baattote kiri sheemaati diro

| Baattote hala'linye Hekitaare tenni | Xeenunni latannoha diro | | Gorsunni latannoha diro | | Diro | | | Baadiyyete baatto aana hoteele, turiizime, industire, Dagoomu owaantenni lawinorinni investe assate ikkiro |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | Hegeraamo kaashsho | Mittu diri kaashsho | Hegeraamo kaashsho | Mittu diri kaashsho | Karso giwirinna | Saadate latishsha | Dubbu latishsha | |
| ≤ 50 | 25 | 20 | 30 | 25 | 25 | 20 | 25 | 35 |
| 51- 150 | 30 | 25 | 35 | 30 | 30 | 25 | 30 | 35 |
| 151-250 | 35 | 30 | 35 | 35 | 35 | 30 | 35 | 35 |
| >251<br><br>Addi ikkitonni fajjinanni baatto heedhuro calla. | 35 | 30 | 35 | 35 | 35 | 35 | 35 | 35 |

**Maqishsha B**

Qoqqowi giddo irshu investimeentera hossannota baadiyyete baatto kiru waagi bikka

| A.k | Woraddate | Kiru waagi bikka (birra) Hekitaaretenni mittu dirira | | | | Xawishsha |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | Umi deerra | | Layinki deerra | | |
| | | Xeenunni latisate | Gorsunni latisate | Xeenunni Latisate | Gorsunni latisate | |
| 1 | Hawaasi quchumi qarqarira, Hawaasi gaangaawi woradira,Wondogennetete woradira | 882 | 1363 | 558 | 902 | |
| 2 | Lokka Abbaayyu, Shabbadiini, Daalle, Aletta cuukko, Aletta wondo, Daarratenna Daarra otilchu woraddara | 663 | 1025 | 429 | 694 | |
| 3 | Arbagooni, Bansi, Hulatenna Booni gaangaawi woraddara | 499 | 771 | 330 | 534 | |
| 4 | Wole gattino woraddara | 375 | 580 | 254 | 411 | |

**Maqishsha C**

Qoqqowi giddo Baadiyye baatto aana hoteele, turiizime, industire, saadate ceatto, dagoomu owaantenni lawinorinni investe assate ikkiro baantanniha baattote kiri waagi bikka

| A.K | Investimeentete dana | Qarqara | Baattote kiri waaga (birra ) | |
|---|---|---|---|---|
| | | | Kaare meetirete ($m^2$) | Hekitaarete |
| 1 | **Turiizimete Investimeente**<br>1.1 Iibballichote qooxeessira loonsanni investimeente | Hawaasi gaangawira, wondo gennetete woradira | 0.7 | 7000 |
| | | Wole woraddara | 0.4 | 4000 |
| | 1.2 Dagoomu paarkewanna agarooshshe assinoonni qarqarira assinanni investimeente | Wo'munku woradira | 0.3 | 3000 |
| | 1.3 Quchumu gobbaanni noo garbuwara assinanni investimeente | Wo'munku woradira | 0.3 | 3000 |
| | 1.4 Wole turistete goshooshshannore/kaasantinno kinna, fooncho, goda, xaggennire amma'note basera assinanni investimeente | Wo'munku woradira | 0.3 | 3000 |
| 2 | **Industirete** | 2.1 Hawaasi quchuminni 55 km faffe noo woradda | 0.7 | 7000 |
| | | 2.2 Aletta wondo, Aletta cuukko, Daarra, Daarra otilcho, Hula, Bansa, Arbegoona, Lokka Abbaayya, Booni gaangaawa, xexichanna labbinno woraddara | 0.5 | 5000 |
| | | 2.1 nna 2.2 gobbaanni noo woraddara | 0.4 | 4000 |
| 3 | **Saadate ceatto** | | 0.3 | 3000 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | 3.1 Adote saada ceattonna dhiika, me’’e, ge’reewo (hoffayiidi saada) ceatto | Wo’munku woradira | 0.3 | 3000 |
| | 3.2 Lukkuwu ceatto | Wo’munku woradira | 0.3 | 3000 |
| | 3.3 Naacha, qulxu’me, diidu ceatto, manchaamete ceatto | Wo’munku woradira | Irshu baattora umi deerrira gorsunni latisate baantanni kiri waaga,bandoonni woradi garinni | |
| | 3.4 Balgudu ceatto, gaalu ceatto | | Irshu baattora layinki deerrira gorsunni latisate baantanni kiri waaga, bandoonni woradi garinni | |

## አባሪ ሀ

### በክልሉ ውስጥ በገጠር መሬት ለሚሰሩ ለተለያዩ ኢንቨስትመንት ዘርፎች የተፈቀደ ከፍተኛ የመሬት ኪራይ የውል ዘመን

| ymÊT SÍT bÿK¬R | bZÂB y¸l¥ ›mT | | ymSñ L¥T ›mT | | QY_ GBRÂ | yXNSúT L¥T | ydN L¥T | bg-R mÊT §Y y¸drg# l@lÖC yç t!L½ yt¶ZM½ yx!NÇST¶½ ¥HbrsB xgLGlÖT wzt. |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | Ì¸ tKL | ›m¬ê tKL | Ì¸ tKL | ›m¬ê tKL | | | | |
| ≤ 50 | 25 | 20 | 30 | 25 | 25 | 20 | 25 | 35 |
| 51- 150 | 30 | 25 | 35 | 30 | 30 | 25 | 30 | 35 |
| 151-250 | 35 | 30 | 35 | 35 | 35 | 30 | 35 | 35 |
| >251<br>ይህም በልዩ ሁኔታ የሚፈቀድ የገጠር መሬት ሲሆን ብቻ ነው፡፡ | 35 | 30 | 35 | 35 | 35 | 35 | 35 | 35 |

## xÆ¶ l

## በክልሉ ውስጥ lXRš x!NvSTmNT y¸WL yg-R mÊT k!‰Y tmN

| t.q! | wrÄ | ›m¬ê! yxND ÿK¬R mÊT yk!‰Y tmN bBR | | | | mGlÅ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1¾ dr© | | 2¾ dr© | | |
| | | በዝናብ የሚለማ | በመስኖ የሚለማ | በዝናብ የሚለማ | በመስኖ የሚለማ | |
| 1 | hêú kt¥ z#¶Ã፤ሀዋሳ ዙሪያ ወረዳ፤ ወንዶገነት ወረዳ፤ | 882 | 1363 | 558 | 902 | |
| 2 | l@µ xÆÃ wrÄ¿ ¹bÄ!ñ wrÄ¿ Äl@ wrÄ¿ xl¬ Œ÷ wrÄ¿ xl¬ wNì½ Ä‰ XÂ Ä‰ åTLÓ wrÄãC | 663 | 1025 | 429 | 694 | |
| 3 | xRb@¯Â wrÄ¿ bNú wrÄ¿ h#§ wrÄÂ ïÂ z#¶Ã wrÄ | 499 | 771 | 330 | 534 | |
| 4 | bl@l@C wrÄãC | 375 | 580 | 254 | 411 | |

**xÆ¶ /**

**በክልሉ ውስጥ bg-R mÊT §Y l¸drg# l፬lÕC ¼yt¶ZM½ yx!NÇST¶Â yXNSúT XRÆ¬ wzt¼ x!NvSTmNèC ›m¬ê ymÊT k!‰Y êU tmN**

| ተ.ቁ | yx!NvSTmNT mSK | xµÆb! | BR bµÊ »TR | BR bÿK¬R |
|---|---|---|---|---|
| 1 | **yt¶ZM x!NvSTmNèC**<br>1.1 FLW¦ãC xµÆb! y¸drg# x!NvSTmNèC | hêœ z#¶Ã XÂ wNìgnT wrÄ | 0.7 | 7000 |
| | | bl፬lÕC wrÄãC | 0.4 | 4000 |
| | 1.2 ብሔራዊ ፓርኮችና ጥብቅ xµÆb!ãC y¸drg# x!NvSTmNèC | bh#l#M wrÄãC | 0.3 | 3000 |
| | 1.3 hYöC¼kkt¥ KLL Wu¼ | bh#l#M wrÄãC | 0.3 | 3000 |
| | 1.4 bl፬lÖC yt¶ST mSHïC ¼TKL DNUY½ ÐÐt½ êšãC½ ¬¶µê yXMnT |F‰ãC wzt¼ | bh#l#M wrÄãC | 0.3 | 3000 |
| 2 | **x!NÇST¶** | 2.1 khêú kt¥ b55 k!lÖ »TR ‰DyS RqT §Y b¸gß# wrÄãC | 0.7 | 7000 |
| | | 2.2 አለታ ወንዶ፤ አለታ ጩኮ፤ ዳራ፤ ዳራ ኦትልቾ፣ ሁላ፤ በንሳ፤ አርቤጎና፤ ሎካ አባያ፤ ቦና ዙሪያ እና ጠጢቻ ወረዳዎች | 0.5 | 5000 |
| | | 2.3 በተራ ቁጥር 2.1 እና 2.2 ከተጠቀሱት ውጪ በሆኑ ወረዳዎች | 0.4 | 4000 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 3 | **yXNSúT XRÆ¬**<br><br>3.1 ywtT kBT :RÆ¬Â ¥DlB ሌሎች እንስሳት በግና ፍየል እርባታ<br>3.2 ì é :RÆ¬ | በሁሉም wrÄãC | 0.3 | 3000 |
| | 3.3 xø½ xú½ NB XRÆ¬Â xœ¥ XRÆ¬ | በሁሉም wrÄãC | bÿK¬R bxNd¾ dr© bmSñ y¸l¥ yXRš mÊT k!‰Y tmN m\rT btqm- ywrÄ DLDL YçÂL | |
| | 3.4 sgÖN XRÆ¬¿ GmL XRÆ¬ | በሁሉም wrÄãC | bÿK¬R bh#l t¾ dr© bmSñ y¸l¥ yXRš mÊT k!‰Y tmN m\rT btqm- ywrÄ DLDL YçÂL | |